# የነፃነት ጌታ

እናት ኢትዮጵያ ሀገሬ ውዲታ
የነፃነት ተምሳል የሁሉ መከታ፣

የጥቁር ህዝብ ግንባር
ከሁሉ ውድ ሀገር፣

ወርቀማው ተፈጥሮሽ
ጋራው ሽንተረርሽ
አእሳፍ ዘሮችሽ ክብሩ ዳርድንበርሽ፣

መች ሆኖ ያውቅና በታሪክ መዛግብት
በባእዳን ገዢ ሆነሽ የቅኝ መሬት፣

ሆነሽ እንጂ መከታ የሣገር ሀሌንታ
የጥቁር ህዝብ ውበት የነፃነት ጌታ፣

ጥንተ ዘመን ኦሪት ስምሽ የተጠራ
አምላክ አንችን ወዶ ዘርሽ እንዲያፈራ
ምንጭ አፍልቆ ሰጥቶሽ ከኤደን ከተራ
በጊዮን ቀድሶሽ ህዝብሽ እንዲፈራ፣

ታሪክ ስልጣኔሽ እኒያ ውብ ሀውልት
እስካሁንም ያሉት ሆነው ባለም ትንግርት፣

እነርሱን የሰሩት ቀዳማይ ልጆችሽ
እንዲህ ሆነሽ ቢያዩሽ የሣሊት መጋዝሸ
ምንኛ ባዘኑ በከሀዲው ፍጡርሽ
ከንቱ መዘበቻ መቀለጃ አድርጎሽ
ታሪክሽን ሊያጠፋው ይኸው ተነስቶብሽ፣

ምንድነው ዝምታ በዚህ ሁሉ ዋይታ
ትእግስትም ልክ አለው የቆረጡ ለታ፣

ብቻ ብቻ ያ ቀን ደርሶ
የምትታይበት ክብርሽ ተመልሶ፣

ሰላምሽን አግኝተሽ የምትኖሪበት
ክብርሽ ተመልሶ የምትገኝበት
ግርማሽ ሁሌም ደምቆ የምታበሪበት፣

ግዜው ሩቅ አይደል ምታገኚበት ድል
ሁሌም ከደጅሽ ነው ከጉያሽ ብቃይ ዘር፣

ዳግም ያቀናሽአል እዲህ ሳትደፊ
በከሀዲው ውሸት በግፍ ሳትገፊ፣

አሉሽ ብርቱ ልጆች ላንቺ የሚወድቁ
ህይወት አሳልፈው ክብር የሚናፍቁ፣

በመኖርሽ ኮርተው
እራሳቸው አልፈው፣ሳንቺም አሳልፈው፣

በስምሽ ሲፃፉ
ዳግም ሳይከፉ፣

እኮ አሉሽ ልጆች የምትኮሪባቸው
እንደጥንቱ ጀግናሽ ዛሬም ውስጥሽ ናቸው፣

እፎይታሽን እንይ ከእንግዲህ ወዲያማ
የስም ወደኋሳ ክፋት ሳይሰማ
ክፉ ዘር ሳይወጣሽ እንደዚህ ጠማማ

ሰንደቅሽም ይውጣ ከፍ ብሎ ይውለብለብ
ቀዳሚ መሆንሽም ባለም እንዲታሰብ
ጠላትሽም ይፈር በቁሙ ይንገብግብ
ላንቺ የወጠነው የርሱን ህይወት ይስለብ፣

ሳትሞቺ ሊቀብርሽ ጉድጓዱን አስፍቶ
ህሊናውን ሸጦ ለጥቅም ተገዝቶ፣

ወገን አስጨርሶ ድሎት ተንተርሶ
የራሱን አብልቶ ሌላውን አራቁቶ
ማንስ ውሎ ሊያድር ባገር መብቱን አጥቶ፤

ፍሬሽን ሰጥተሻል
አብዝሽ ፈጥረሻል
በተፈጥሮም ቢሆን ከጥንት ታድለሻል
በቅዱስ መፅሐፍም ስምሽ ወጥቶልሻል፣

አንቺ ምን ታደርጊ ሁሉን አፍርተሻል
ክፉን ከደግ ሳትለዪ ባአንድ አኑረሻል፣

ይሄ ግን ልዩ ነው ተንኮል የተካነ
በንፁህ ልጆችሽ ደምም የጨከነ፣

ግንአለው መፍትሄ እርሱን የሚያጠፋ
አይደሉም መንግስታት ያንቺ ውጥን ተስፋ፣

ጠባቂሽ ልጅሽ ነው የህዝብሽ ሀሌንታ
ቀዳማይ ነፃ ህዝብ የአርነት ዋልታ
ለጨቃኞች መከር የህዝቦች መከታ
የኢትዮጵያ ክብር! የታሪክ እውነታ
የጥቁር ህዝብ ውበት የነፃነት ጌታ!!!

***<u>ከዘምሳሌ ተፃፈ</u> _ መታሰቢያ በኢትዮጵያ ውስጥ ያለውን ዘረኛ አገዛዝ ለሚታገሉ ይሁን!***